**የቆላስይስ እና ኤፌሶን ጥናት 7**

ቆላ 3፡20-4፡1-18 ኤፌሶን 6፡1-9

ባለፈው ጥናት በባልና በሚስት መካከል በሚኖር ግንኙነት እንዴት መንፈሳዊ እድገት እንደሚታይ አይተናል በዛሬው ጥናት ደግሞ በወላጅና በልጆች እንዲሁም በሰራተኛና አሰሪ መካከል እንዲሁም ከውጭ ባሉት ወይም አማኝ ባልሆኑ ሰዎች ጋር እንዴት መመላለስ እንዳለብን ባለን ግንኙነት ውስጥ በሚኖር መንፈሳዊ እድገት ክርስቶስ እነዴት እንደሚታይ እንመለከታለን፡፡

**ርዕስ፡ የተወደደ**

ይህን ክፍል ስታነቡ ጳውሎስ ምን እንደሚመክር ምን አይነት የፀሎት ርዕስ እንደሚያቀርብ ምን አይነት መረጃ እንደሚያስተላልፍ እዩ እንዲሁም አንድ አማኝ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ከሰው (አማኝ እና አማኝ ያልሆኑ) ጋር ከእግዚአብሔር ጋር እዴት መኖር እንዳለበት የሚገልፁ ቃላቶችንም ተመልከቱ

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ክርስቶስ በልጆችና ወላጆች መካከል እንዴት ይገለጣል?
2. ልጆች ሲበሳጩ እንዴት ይገለጣል ይህም ክፍል ስለዚህ ሲናገር ምን ማለቱ ነው?
3. ክርስቶስ በሪያና በጌታ/አሰሪና ሰራተኛ መካከል እንዴት ይገለጣል?
4. ባሪያ ናችሁ ወይስ ጌቶች ናችሁ/አሰሪ ናችሁ ወይስ ሰራተኞች?
5. ለሰው መገዛት እንዴት ለጌታ እንደመገዛት ወይም ማገልገል ሊቆጠር ይችላል?
6. ስለ ቃሉ ደጅ መከፈት ሲናገር ምን ማለቱ ነው?
7. ለናንተ የተወደደ ወንድም እንዴት ይገለፃል?
8. በዚህ ክፍል ውስጥ ሥማቸው የተጠቀሱትን 10 ሰዎች ከእነ ባህሪያቸው ከነሥራቸው ከነአገልግሎታቸው ዘርዝሩ፡፡

**መተግበር (Application)**

- ሰዎች ጋር ያላችሁ ንግግር ምን ይመስላል በጨው እንደተቀመመ ሲል ምን አይነት ንግግር እንድንናገር ያሳያል ?
- በእግዚአብሄር መንግስት ሥራ ላይ ከማን ጋር ትሰራላችሁ ማንስ ከናንተ ጋር ይሰራል?
- ሌሎች ወይ እናንተ ፍፁማን ሆናችሁ እንድትቆሙ ትፀልያላችሁ?
- ከጌታ የተቀበላችሁት አገልግሎት ምን ምን እንደሆነ ተመልከቱ ምን ዐይነት ጥንቃቄ እያደረጋችሁ እንደሆነም እዩ?

► የዛሬው ጥናት ምን ምን ነገሮችን እንድናደርግ ያዘናል?

በእግዚአብሔር መንግሥት ከእኔ ጋር አብረው የሚሠሩት እነዚህ ብቻ ናቸው